# የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

## የ2001 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ማጠቃለያ፣

የ2001 በጀት ዓመት የሲሰማፐ ዕቅድ አፈጻጸም፣

### 1. መሠረ ዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት በማጠናቀቅ ወደ ተግባር ማሸጋገር፣

በ2001 በጀት ዓመት የሚኒስቴር መ/ቤቱን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናቶችን በተሟላ ደረጃ ለማጠናቀቅ፣ ጥናቱን ለመተግበር የሚያግዙ የአሰራር ማኑዋሎች/መመሪያዎች/ቅጾች ለማዘጋጀት፣ተቋማዊ አደረጃጀትን ሂደ ዊ ለማድረግ፣ የመ/ቤቱን የሰው ይል ኦዲት በማድረግ ምደባ ለማካሄድና የተመደቡ ሠራተኞችን በስልጠና ለማብቃት፣ የለውጥ ኃይሎችን ለማፍራት፣ በጥናቱ ውጤት መሠረት አመቺ የቢሮ አደረጃጀት ለመፍጠር እና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ሁኔታዎች በማሟላት ትግበራውን በይፋ በማሳወቅ ለመጀመር፣ የትግበራውን ሂደት በባለቤትነት ለመምራት፣ ለመከ ተል፣ ሥራዎች በተለወጠው አሰራር ብቻ የወጣላቸውን ደረጃ (Standard) ጠብቀው ንዲከናወኑ ለማድረግ እና ውሳኔዎችን በወቅቱ በመስጠት ለመደገፍ የታቀዱ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2001 በጀት ዓመት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 1.1 የጥናቱ አመራርና አደረጃጀት፣

- የለውጡን ሥራ በየጊዜው የሚከታተልና የሚመራ ስምንት አባላት ያሉበት (የበላይ አመራርና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች) አቢይ ኮሚቴ ተቋቁሟል፣ እንዲሁም የጥናቱ አስተባባሪ/ቴሣር በበላይ አመራር ደረጃ ተሰይሟል፣
- የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅት፣ የIT እና የቢሮ አደረጃጀት፣ የሰው ኃይል ምደባ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል፣

## 1.2 ጥናቶቹን በተሟላ ደረጃ ማጠናቀቅ፣

- የመ/ቤቱ ሦስት ዋና የሥራ ሂደቶች እና ሰባት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ጥናት የተጠናቀቀ ሲሆን፣

  እነዚህም፡-

  ሀ/ ዋና የሥራ ሂደቶች፣

  - ሠላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነት ማስጠበቂያ፣
  - የሥራ ስምሪት አገልግሎት ማስፋፊያ፣
  - የማኅበራዊ ደህንነት ልማት ማስፋፊያ እና

  ለ/ ደጋፊ የሥራ ሂደቶች፣

  - የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር፣
  - የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር፣
  - የዕቅድ ዝግጅት፣ የለውጥ ትግበራ ክትትልና ግምገማ፣
  - የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን፣
  - የሕግ አገልግሎት፣
  - የኦዲት አገልግሎት እና
  - የመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር
  - የሴቶች ጉዳይ

ናቸው።

## 1.3 የኮሚኒኬሽን ሥራዎች፣

የፌዴራል መ/ቤቱና የክልል ቢሮዎች በዘርፉ በጋራና በተናጠል የተሰጣቸውን ኃላፊነቶች በብቃት በመወጣት ለደንበኞቻቸው ዕርካታ ማስገኘት እንዲችሉ የሁለቱ አካላት የሥራ ሂደቶች ጥናት ተቀናጅተውና ተናበው ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እና በዘርፉ ከቤንች-ማርክ ጥናት የተገኙ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ ከክልል ቢሮዎች፣ ከአሰሪዎችና ሠራተኛ ማህበራት (Social Partners) እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ደንበኞች የተገኙበት የምክክር መድረኮች በመፍጠር ከመድረኮቹ በተገኙ ግብዓቶች ጥናቶቹ እንዲዳብሩ ከመደረጉም በላይ የጥናቶቹን ውጤቶች በፌዴራል ደረጃ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ለሚያስተባብረው ብሄራዊ የስቲሪንግ ኮሚቴ በማቅረብና

በማስገምገም በኮሚቴው በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎባቸው የመጨረሻ መልክ እንዲይዙ ተደርጓል፡፡

## 1.4 የሰው ሀብት ሥራ አመራር፣

- የሰው ኃይል ድልድልና ምድባ ከመፈጸሙ በፊት ሠራተኞች በመ/ቤቱ በተካሄዱ የBPR ጥናት ውጤቶች እና በመንግስት ፖሊሲዎችና የልማት ስትራቴጂዎች ላይ ተገቢውን ግንዛቤ ይዘው ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ለ19 ተከታታይ ቀናት በሁለት ዙር ለሁሉም ሠራተኞች እንዲሰጡ ተደርጓል፣
- ሂደትን መሠረት ያደረገ (Process-based) አደረጃጀት እና የየሥራ ሂደቶች ተግባርና ኃላፊነቶች ተለይተው እንዲዘጋጁ ተደርጓል፣
- የየሥራ ሂደቶቹ የሰው ኃይል ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ጊዜያዊ የሠራተኛ ምደባ ተከናውኗል፣
- የሠራተኛ ምደባ ግልጽነት ያለው አሰራርን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ በምደባው ቅሬታ ያላቸው ሠራተኞች ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት ሥርዓት ተዘርግቷል፣

## 1.5 የጥናቱ የትግበራ መመሪያዎችና ማኑዋሎች ዝግጅት፣

- የተቋሙ የለውጥ ሥራ አመራር ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፣
- የ10 የሥራ ሂደቶች የጥናት ትግበራ ማኑዋሎች እና ቲም ቻርተሮች ተዘጋጅተዋል፣
- የተቋሙ የሰው ኃይል ምደባ መመሪያ ሠራተኞችን ባሳተፈ መልኩ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ውሏል፣
- የሴቶች ጉዳይን የBPR ጥናት በተመለከተ ቡድን ተቋቁሞ በመሠራት ላይ ይገኛል፡፡

## 1.6 የቢሮ አደረጃጀት፣

- በጥናቶቹ ውጤት መሠረት ደንበኞች በአንድ ማዕከል ቀልጣፋ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የቢሮ አደረጃጀትና ድልድል ተከናውኗል፣

## 1.7 <u>የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅት</u>፣

በጥናቱ ውጤት መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያስፈጽማቸው ሁለት አዋጆች ማለትም፤

- ✓ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ረቂቅ ማሻሻያ ተዘጋጅቷል፤
- ✓ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ አጀንሲ አዋጅ ቁጥር 104/94 በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲፀድቅ ተደርጓል፣

## 1.8 <u>የለውጥ ኃይሎችን መለየትና ማፍራት</u>፣

- ሠራተኛው በአጠቃላይ የመንግስት ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም በተቋሙ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናቶች ላይ ተገቢውን ግንዛቤ ጨብጦና የራሱ አድርጎ ወደ ሥራ በመግባቱ በዚህ ረገድ ያለው ተነሳሽነትና ዝግጁነት መታየት መቻሉ፣
- ሠራተኛው በተመደበበት የሥራ ሂደት የተቀመጡትን ግቦችና የአሰራር ስታንዳርዶች መሠረት በማድረግ ውጤት ለማስመዝገብ እያሳየ ያለው ያላሰለሰ ጥረት፣
- በመ/ቤቱ በተካሄዱ የተለያዩ የሥራ ሂደቶች ጥናት፣ ሕጎች፣ መመሪያዎችና ማኑዋሎች ዝግጅት ላይ ባለው አቅም ሁሉ በመሳተፍ ለእነዚሁ መጠናቀቅ ያበረከተው ድርሻ፣
- ለውጡን ወደ ተግባር ለማሸጋገር በመ/ቤቱ በተቋቋሙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች (የሰው ኃይል ምደባ፣ የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅት፣ በIT እና ቢሮ አደረጃጀት) በመሳተፍ ኃላፊነቱን በትጋት መወጣት መቻሉ፣

በዝርዝር ሲገመገም መ/ቤቱ የለውጥ ኃይሎችን በመለየትና በማፍራት ረገድ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የሚያበረታታ ሲሆን በተለይ አሁን በሙከራ ትግበራ ወቅትና ወደሙሉ ትግበራ ሲሸጋገር በሥራ እየተፈተነና እየተገመገመ የተሻለ የለውጥ ሠራዊት ለማፍራት አመራሩ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል።

## 1.9 <u>የጥናቱ ሙከራ ትግበራ፣ ክትትልና ድጋፍ</u>፣

- በመ/ቤቱ ጥናት በተደረገባቸው ሦስት ዋና የሥራ ሂደቶችና ሰባት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ላይ የሙከራ ትግበራ እንዲጀመር ተደርጓል፣

- የጥናቶቹ ትግበራ ቀጣይነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ በተቋሙ በተዘረጋው አጠቃላይ የለውጥ ትግበራ ሥራ አመራር ስትራቴጂ መሠረት በበላይ አመራሩና በማኔጅመንት ቲም በቋሚነት የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ ለውጡን በባለቤትነት የሚከታተል፣ የሚያስተባብርና ድጋፍ የሚሰጥ የለውጥ ትግበራ ሥራ አመራር ከዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ የሥራ ሂደት ጋር ተቀናጅቶ እንዲደራጅ ተደርጎ አስፈላጊው እየተከናወነ ይገኛል፣

## 1.10. <u>የመ/ቤቱን ሥራዎች በIT መደገፍ</u>፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የመ/ቤቱን ሥራዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለመደገፍ በታቀደው መሠረት፡-

- ከተጠቃሚዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ሎካል ኤርያ ኔትወርኩ ተሻሽሎ ለ38 ሴት ና 22 ወንድ በድምሩ ለ60 ሰራተኞች በሚሠሩበት ቦታ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፣
- የውስጥ ቅንጅ ዊ አሠራርን ለማጎልበት በተፈጠረው ኢንትራኔት ላይ የአቅም ማሻሻያ ተደርጓል፣
- በ2001 በጀት ዓመት አዲስ ፈቃድ እና የፈቃድ እድሳት ያገኙ የ6396 የውጭ አገር ዜጎች መረጃ በኮምፒዩተር ተይዞ ለጥቅም ለማዋል በሚቻልበት መልኩ ተጠናቅሯል፣
- የማህበራት ምዝገባ ሰራዎችን የሚሰራ ሶፍትዌር ቀዳሚ ስራ የሆነውን የpreliminary Investigation ስራ ተሠርቷል፣
- ለ11 ሴት ና 34 ወንድ በድምሩ ለ45 የመ/ቤቱ ሠራተኞች የPower Point ስልጠና ተሰጥቷል፣
- ለተጠቃሚዎች መድረስ ያለባቸው መረጃዎች ከመ/ቤቱ የስራ ክፍሎችና ከሁሉም የክልል ቢሮዎች ተሰብስበው በመ/ቤቱ ድህረ ገጽ ላይ ንዲሠፍሩ ተደርጓል::

***የፖሊሲ ሰነዶችን ማዘጋጀትን በተመለከተ፡-*** የስራ ስምሪትንና የሙያ ጤንነትና ከአለም ስራ ድርጅት ጋር በመተባበር ለስራ ስምሪት ፖሊሲ መነሻ የሚሆን ሀገር አቀፍ የሆነ

ጥናት በአማካሪዎች አስጠንቶ ሁለት የምክክር ወርክሾፖች ተዘጋጅተው ሰነዱ እንዲዳብር ተደርጓል:: ብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲን ለማዘጋጀት እንዲረዳ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የሙያ ጤንነትና ደ ንነት አጠቃላይ ሁኔ የሚያሳይ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ጉዳዩ የሚመለከ ቸው አካላት በተሳተፉበት የምክክር አውደ ጥናት እንዲዳብር ተደርጓል።

***የአዋጅ ማሻሻያና የአፈጻጸም ደንብ ዝግጅት በተመለከተ፡-*** የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ማሻሻያ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ድንጋጌዎች ተለይተው ወጥተዋል። የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች አዋጅ 104/90 የማሻሻያ ዝግጅቱ ተጠናቅቆ ንዲፀድቅ ተደርጓል፣ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቀጥር 377/96 አንቀጽ 3(ሐ) ላይ ስለ ግል አገልግሎት የስራ ሁኔ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ንደሚያወጣ በተደነገገው መሰረት ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለአስተያየት ተሰራጭቷል።

***ኮንቬንሽንና መርሃ ግብሮችን በተመለከተ፡-*** የአካል ጉዳተኞች መርሃግብር ማስፈፀሚያ ካውንስሎች በትግራይ፣ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላና በቤንሻጉል፣ የአረጋውያን የድርጊት መርሐግብር አስፈጻሚ ፎረሞች በኦሮሚያና በአዲስ አበባ ክልሎች ተቋቁመዋል። የቤተሰብ የድርጊት መርሐግብር ዝግጅትን በተመለከተ መርሃ ግብሩን በረቂቅ ደረጃ የማዘጋጀቱ ስራ ተጠናቆ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት በአስተያየት ለማዳበር ዓውደጥናት ተዘጋጅቷል።

***ጥናትን በተመለከተ፡-*** የሴቶችንና የወጣቶችን የስራ ሁኔ መመሪያ አፈጻጸም እና ብሄራዊ የሙያ በሽታ ዝርዝር አፈፃፀም የሚመራበትን ጋይድላይን መረጃ ተሰብስቦ ተተነትኖና ተጠናቅሮ የጥናቱ ሪፖርት ተዘጋጅቷል። የሙያ ደህንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ ጥበቃ መመሪያ አፈጻጸምን በተመለከተ በኮንስትራክሽንና በ ርሻ ኢንዱስትሪ ዘርፎች የቁጥጥር ፎርማቶች/ቼክ ሊስቶች/ ከየሴክተሩ ነባራዊ ሁኔ አንጻር በዝርዝር ፍተሻ ተደርጎበት ሪፖርት ተዘጋጅቷል:: በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የኀብረተሰብ ክፍሎችን ለመርዳትና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል የማኀበራዊ ድጋፍ ፈንድ ማቋቋሚያ ጥናት ዝርዝር TOR ተዘጋጅቷል።

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ኢንሹራንስ መግባት የሚገባቸውን ድርጅቶች መለያ ጥናት፣ በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋና በኦሮሚያ የሚገኙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይና በሙያ ጤንነትና ደኅንነት ረገድ ያላቸውን የሥልጠና ፍላጎት መለያ ጥናት፣ በእርሻ ላይ ወቅታዊ የጉልበት ሠራተኛ እጥረት የሚያጋጥማቸው ክልሎች /በአማራ/በመተማ/ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ጥናት ተካሂዶ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን አስመልክቶ ብሔራዊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መከላከያና መቆጣጠሪያ ረቂቅ መርሃ ግብር NPA በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

***ስልጠናን በተመለከተ፣*** በአሠሪና ሠራተኛ መብትና ግዴታዎች፣ የሁለትዮሽ አሠራርን ለማስረጽ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሥራ ቦታ ለመከላከል የአሠልጣኞች በሙያ ደኅንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ፣ በአሠሪና ሠራተኛ አስተዳደር በስልጠና አሰጣጥ ስልቶች ፣ በዘመናዊ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም የሕፃናት ጉልበት ሥራን በተመለከተ ከተለያዩ የሚዲያ ድርጅቶች ለተውጣጡ በዘገባ አፃፃፍ፣ ሴቶችን በሚመለከት በወጡ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ስምምነቶች፣ መርሐ ግብሮች ላይ፣ በጋብቻና ቤተሰብ አመራርና ምክር ማንዋል ላይ፣ በፕሮጀክት ዝግጅት፣ ክትትል እና ግምገማ ላይ፣ እና በኮምፒዩተርና ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ አካላት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

***አውደ ጥናትን በተመለከተ፡-*** ብሔራዊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መከላከያና መቆጣጠሪያ መርሐ ግብር ዝግጅትን በተመለከተ በሥራ ቦታ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ የፖሊሲ ማዕቀፍ ማስተዋወቂያ፣ የአካል ጉዳተኞች የሥራ ሥምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000 የማስተዋወቂያ ግንዛቤ ማሳደጊያ አውደ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡

***ግንዛቤን ማዳበሪያ ሥራዎችን በተመለከተ፡-*** ስለ ግል የግልግል ዳኝነት አመሠራረትና የአሠሪ ማኅበራትን በተጠናከረ መንገድ ማደራጀትን በተመለከተ የግንዛቤ ማሳደጊያ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ ተሰራጭቷል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ የልመናን አስከፊነት በተመለከተ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ በልመና የተሰማሩ

ዜጎችን መልሶ ስለማቋቋም በፌዴራል ደረጃ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ተሰጥተዋል፣ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ተከብሯል፡፡

*የሥራ ፈቃድ አገልግሎትን በተመለከተ፡-* ለ21269 በኤጀንሲዎችና በግል ጥረታቸው ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለሄዱ ኢትዮጵያውያን የመረጃና የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል ፡፡ እንዲሁም አስፈላጊው ፎርማሊቲ ተሟልቶ ተመዝግበዋል፡፡ ለ16818 ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለሚሰሩ የውጭ አገር ዜጎች አዲስ የሥራ ፈቃድ፣ እድሳት እና ሥራቸውን ለጨረሱ የክሊራንስ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 104/90 መሠረት ዜጎችን ከኢትዮጵያ ውጭ በሥራ ለማሰማራት እንዲችሉ ለ20 ኤጀንሲዎችና በአገር ውስጥ ሥራና ሠራተኛን ለማገናኘት ፈቃድ ለጠየቁ 9 ኤጀንሲዎች የሥራ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን ለ28 ኤጀንሲዎች የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ተከናውኗል፡፡ ከአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ጋር በአዋጅ 104/90 አፈፃፀም ዙሪያ ውይይት ተካሂዷል፡፡

*ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን በተመለከተ፡-* በ14 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የመጀመሪያ ደረጃ፣ በ6 ድርጅቶች የመከ ያ ቁጥጥሮች ተካሂደዋል፡፡ ሕገ ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል ለክልል ቢሮዎች በየክልላቸው ተመድበው የሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች ቁጥጥርና ክትትል እንዲያደርጉ ከሚ/ር መ/ቤቱ መረጃ ተሰራጭቷል፡፡ ማኅበራትን፣ ኅብረት ስምምነትንና የሥራ ክርክርን አስመልክቶ ለችግሮቹ መፍትሔ አመላካች አቅጣጫ ተቀይሷል:: የሶስትዮሽን የምክክር መድረክ ወይም በብሄራዊ የአሠሪና ሠራተኛ ቦርድ በመደበኛነት ስብሰባ ተካሂዷል፡፡ በተመሳሳይም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርዶች ባልተጠናከሩባቸዉ በጋምቤላና አፋር ቦርዶቹ እንዲጠናከሩ ከክልል አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ወሳኝ ቦርዶቹ ወደስራ ንዲገቡ ተደርጓል ፡፡ እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት የሚሰጡ ኤጀንሲዎች ረቂቅ ፕሮፋይል ተዘጋጅቷል፡፡ ፈቃድ ባላቸዉ 73 ኤጀንሲዎች ላይ ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማቶች በማዘጋጀት በ78 ኤጀንሲዎች ላይ ሪፖርት ተሰባስቧል፡፡

ብሔራዊ የልመና ማስወገጃ ሥራን ተቋማዊ በሆነ መንገድ በዘላቂነት ለማካሄድ እንዲያስችል በትግራይ ፣ በአማራ ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ በድሬዳዋ ክልሎች የልመና መልሶ ማቋቋሚያ ተግባራትን የሚያስተባብሩ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል፡፡ እንዲሁም

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ባለሃብቶች የተካፈሉበት ሁለት የምክክርና የገቢ ማስገኛ መድረኮች ተካሂደዋል፡፡

***መረጃን በተመለከተ፡-*** በአጠቃላይ መረጃን በተመለከተ የማንዋል አሠራርን ለማስቀረት መረጃዎች ንደቀረቡ በኮምፒዩተር ኢንኮድ ተደርገው ንዲያዙ ተደርጓል፡፡ በዚሁም አሠራር በበጀት ዓመቱ ውስጥ አዲስ ፈቃድና የፍቃድ ዕድሳት ያገኙ የ21269 የውጭ አገር ዜጎች መረጃ ተይዞ ለጥቅም ለመዋል በሚችልበት መልኩ ተጠናቅሯል፡፡ መደበኛ በሆኑ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ወቅ ዊ የሥራ ገበያ መረጃ ተሰባስቦና ተጠናቅሮ የ2000 ዓ.ም የሥራ ገበያ መረጃ መጽሄት ተዘጋጅቷል፡፡ በድህረ ገጽ አማካኝነት ለተጠቃሚዎች መድረስ ያለባቸው መረጃዎች ከመ/ቤቱ የስራ ክፍሎችና ከሁሉም የክልል ቢሮዎች ተሰብስበው በመ/ቤቱ ድ ረ ገጽ ላይ ንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡

***የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ-*** ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከተመደበለት መደበኛ በጀት ብር 8,602,800 ውስጥ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብር7,832,021.34 ወይም የዕቅዱ 93% በሥራ ላይ ውሏል ፡፡

***የሰው ይል አጠቃቀምን በተመለከተ-*** ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በመዋቅር ከተፈቀደው የሰው ይል ውስጥ ስከ ሰኔ ወር መጨረሻ ድረስ 88 (56 ወንድ 32 ሴት) ከፍተኛና መካከለኛ ባለሙያዎች ና 211 (81 ወንድ 130 ሴት) ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 299 ሠራተኞች ይገኛሉ፡፡

## *በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ የመፍትሔ እርምጃዎች፣*

የሚኒስቴር መ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ትብብር አነስተኛ መሆን፣ ሲሆኑ ችግሩን ለመፍታት ክፍት የሥራ ቦታዎችን ከገበያ ለመሙላት እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች የመመቻቸት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ውስጥ እንዲካተት ጥረት ተደርጓል፡፡

# የ2001 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ

### የመ/ቤቱ ራዕይ

የሥራ ዕድል የተስፋፋበት፣ የኢንዱስትሪ ሰላም የሰፈነባትና የኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ደህንነት የተጠበቀባት ኢትዮጵያን ማየት፣

### የመ/ቤቱ ተልዕኮ

በአገር አቀፍ ደረጃ ጉዳዩ የሚመለከ ቸውን አካላት በማሳተፍና በመቀናጀት፣ በሴክተሩ ጥናቶችንና ምርምሮችን በማካሄድ፣ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት፣ አፈፃፀማቸውን በመከ ተልና የሴክተሩን የማስፈፀም አቅም በመገንባት:-

- ሠላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነት ንዲኖር፣ የሠራተኛው ጤንነትና ደህንነት ንዲጠበቅ፣ የሥራ አካባቢዎች ንዲሻሻሉና የሥራ ስምሪት አገልግሎት ንዲስፋፋ ንዲሁም፣

- የጋብቻ ሥርዓት ንዲጠናከር፣ የቤተሰብ ደህንነት ንዲጠበቅና የአረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች ማኅበራዊ ደኅንነት ልማት አገልግሎት ንዲስፋፋ ማድረግ ነው::

በዚሁ መሠረት በ2001 በጀት ዓመት ውስጥ (ከሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ስከ ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም) የሚኒስቴር መ/ቤቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## የ2001 በጀት ዓመት የሲሰማፐ ዕቅድ አፈጻጸም፣

1. **መሠረ ዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት በማጠናቀቅ ወደ ተግባር ማሸጋገር፣**

በ2001 በጀት ዓመት የሚኒስቴር መ/ቤቱን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናቶችን በተሟላ ደረጃ ለማጠናቀቅ፣ ጥናቱን ለመተግበር የሚያግዙ የአሰራር ማኑዋሎች/መመሪያዎች/ቅጾች ለማዘጋጀት፣ተቋማዊ አደረጃጀትን ሂደ ዊ ለማድረግ፣ የመ/ቤቱን የሰው ይል ኦዲት በማድረግ ምደባ ለማካሄድና የተመደቡ ሠራተኞችን በስልጠና ለማብቃት፣ የለውጥ ኃይሎችን ለማፍራት፣ በጥናቱ ውጤት መሠረት አመቺ የቢሮ አደረጃጀት ለመፍጠር እና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ሁኔታዎች በማሟላት

ትግበራውን በይፋ በማሳወቅ ለመጀመር፣ የትግበራውን ሂደት በባለቤትነት ለመምራት፣ ለመከ ተል፣ ሥራዎች በተለወጠው አሰራር ብቻ የወጣላቸውን ደረጃ (Standard) ጠብቀው ንዲከናወኑ ለማድረግ እና ውሳኔዎችን በወቅቱ በመስጠት ለመደገፍ የታቀዱ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2001 በጀት ዓመት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 1.1. <u>የጥናቱ አመራርና አደረጃጀት፣</u>

- የለውጡን ሥራ በየጊዜው የሚከታተልና የሚመራ ስምንት አባላት ያሉበት (የበላይ አመራርና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች) አቢይ ኮሚቴ ተቋቁሟል፣ እንዲሁም የጥናቱ አስተባባሪ/ቴሜር በበላይ አመራር ደረጃ ተሰይሟል፣
- የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅት፣ የIT እና የቢሮ አደረጃጀት፣ የሰው ኃይል ምደባ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል፣

## 1.2. <u>ጥናቶቹን በተሟላ ደረጃ ማጠናቀቅ</u>፣

- የመ/ቤቱ ሦስት ዋና የሥራ ሂደቶች እና ሰባት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ጥናት የተጠናቀቀ ሲሆን፣
  እነዚህም፡-

ሀ/ <u>ዋና የሥራ ሂደቶች</u>፣

- ሠላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነት ማስጠበቂያ፣
- የሥራ ስምሪት አገልግሎት ማስፋፊያ፣
- የማኅበራዊ ደህንነት ልማት ማስፋፊያ እና

ለ/ <u>ደጋፊ የሥራ ሂደቶች</u>፣

- የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር፣
- የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር፣
- የዕቅድ ዝግጅት፣ የለውጥ ትግበራ ክትትልና ግምገማ፣

- የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን፣
- የሕግ አገልግሎት፣
- የኦዲት አገልግሎት እና
- የመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር
- የሴቶች ጉዳይ

ናቸው፡፡

## 1.3. የኮሚኒኬሽን ሥራዎች፣

የፌዴራል መ/ቤቱና የክልል ቢሮዎች በዘርፉ በጋራና በተናጠል የተሰጣቸውን ኃላፊነቶች በብቃት በመወጣት ለደንበኞቻቸው ዕርካታ ማስገኘት እንዲችሉ የሁለቱ አካላት የሥራ ሂደቶች ጥናት ተቀናጅተውና ተናበው ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እና በዘርፉ ከቤንች-ማርክ ጥናት የተገኙ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ ከክልል ቢሮዎች፣ ከአሰሪዎችና ሠራተኛ ማህበራት (Social Partners) እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ደንበኞች የተገኙበት የምክክር መድረኮች በመፍጠር ከመድረኮቹ በተገኙ ግብዓቶች ጥናቶቹ እንዲዳብሩ ከመደረጉም በላይ የጥናቶቹን ውጤቶች በፌዴራል ደረጃ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ለሚያስተባብረው ብሄራዊ የስቲሪንግ ኮሚቴ በማቅረብና በማስገምገም በኮሚቴው በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎባቸው የመጨረሻ መልክ እንዲይዙ ተደርጓል፡፡

## 1.4. የሰው ሀብት ሥራ አመራር፣

- የሰው ኃይል ድልድልና ምድባ ከመፈጸሙ በፊት ሠራተኞች በመ/ቤቱ በተካሄዱ የBPR ጥናት ውጤቶች እና በመንግስት ፖሊሲዎችና የልማት ስትራቴጂዎች ላይ ተገቢውን ግንዛቤ ይዘው ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ለ19 ተከታታይ ቀናት በሁለት ዙር ለሁሉም ሠራተኞች እንዲሰጡ ተደርጓል፣

- ሂደትን መሠረት ያደረገ (Process-based) አደረጃጀት እና የየሥራ ሂደቶች ተግባርና ኃላፊነቶች ተለይተው እንዲዘጋጁ ተደርጓል፣

- የየሥራ ሂደቶቹ የሰው ኃይል ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ጊዜያዊ የሠራተኛ ምደባ ተከናውኗል፣

- የሠራተኛ ምደባ ግልጽነት ያለው አሰራርን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ በምደባው ቅሬታ ያላቸው ሠራተኞች ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት ሥርዓት ተዘርግቷል፣

## 1.5. የጥናቱ የትግበራ መመሪያዎችና ማኑዋሎች ዝግጅት፣

- የተቋሙ የለውጥ ሥራ አመራር ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፣

- የ10 የሥራ ሂደቶች የጥናት ትግበራ ማኑዋሎች እና ቲም ቻርተሮች ተዘጋጅተዋል፣

- የተቋሙ የሰው ኃይል ምደባ መመሪያ ሠራተኞችን ባሳተፈ መልኩ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ውሏል፣

- የሴቶች ጉዳይን የBPR ጥናት በተመለከተ ቡድን ተቋቁሞ በመሠራት ላይ ይገኛል፡፡

## 1.6. የቢሮ አደረጃጀት፣

- በጥናቶቹ ውጤት መሠረት ደንበኞች በአንድ ማዕከል ቀልጣፋ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የቢሮ አደረጃጀትና ድልድል ተከናውኗል፣

## 1.7. የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅት፣

በጥናቱ ውጤት መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያስፈጽማቸው ሁለት አዋጆች ማለትም፤

- ✓ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ረቂቅ ማሻሻያ ተዘጋጅቷል፤

- ✓ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ አጀንሲ አዋጅ ቁጥር 104/94 በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲፀድቅ ተደርጓል፣

## 1.8. የለውጥ ኃይሎችን መለየትና ማፍራት፣

- ሠራተኛው በአጠቃላይ የመንግስት ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም በተቋሙ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናቶች ላይ ተገቢውን ግንዛቤ ጨብጦና የራሱ አድርጎ ወደ ሥራ በመግባቱ በዚህ ረገድ ያለው ተነሳሽነትና ዝግጁነት መታየት መቻሉ፣

- ሠራተኛው በተመደበበት የሥራ ሂደት የተቀመጡትን ግቦችና የአሰራር ስታንዳርዶች መሠረት በማድረግ ውጤት ለማስመዝገብ እያሳየ ያለው ያላሰለሰ ጥረት፣

- በመ/ቤቱ በተካሄዱ የተለያዩ የሥራ ሂደቶች ጥናት፣ ሕጎች፣ መመሪያዎችና ማኑዋሎች ዝግጅት ላይ ባለው አቅም ሁሉ በመሳተፍ ለእነዚሁ መጠናቀቅ ያበረከተው ድርሻ፣

- ለውጡን ወደ ተግባር ለማሸጋገር በመ/ቤቱ በተቋቋሙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች (የሰው ኃይል ምደባ፣ የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅት፣ በIT እና ቢሮ አደረጃጀት) በመሳተፍ ኃላፊነቱን በትጋት መወጣት መቻሉ፣

በዝርዝር ሲገመገም መ/ቤቱ የለውጥ ኃይሎችን በመለየትና በማፍራት ረገድ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የሚያበረታታ ሲሆን በተለይ አሁን በሙከራ ትግበራ ወቅትና ወደሙሉ ትግበራ ሲሸጋገር በሥራ እየተፈተነና እየተገመገመ የተሻለ የለውጥ ሠራዊት ለማፍራት አመራሩ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል።

## 1.9. የጥናቱ ሙከራ ትግበራ፣ ክትትልና ድጋፍ፣

- በመ/ቤቱ ጥናት በተደረገባቸው ሦስት ዋና የሥራ ሂደቶችና ሰባት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ላይ የሙከራ ትግበራ እንዲጀመር ተደርጓል፣

- የጥናቶቹ ትግበራ ቀጣይነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ በተቋሙ በተዘረጋው አጠቃላይ የለውጥ ትግበራ ሥራ አመራር ስትራቴጂ መሠረት በበላይ አመራሩና በማኔጅመንት ቲም በቋሚነት የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ ለውጡን በባለቤትነት የሚከታተል፣ የሚያስተባብርና ድጋፍ የሚሰጥ የለውጥ ትግበራ ሥራ አመራር ከዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ የሥራ ሂደት ጋር ተቀናጅቶ እንዲደራጅ ተደርጎ አስፈላጊው እየተከናወነ ይገኛል፣

## 2. የመ/ቤቱን ሥራዎች በIT መደገፍ፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የመ/ቤቱን ሥራዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለመደገፍ በታቀደው መሠረት፡-

- ከተጠቃሚዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ሎካል ኤርያ ኔትወርኩ ተሻሽሎ ለ38 ሴት ና 22 ወንድ በድምሩ ለ60 ሰራተኞች በሚሠሩበት ቦታ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፣
- የውስጥ ቅንጅ ዊ አሠራርን ለማጎልበት በተፈጠረው ኢንትራኔት ላይ የአቅም ማሻሻያ ተደርጓል፣
- በ2001 በጀት ዓመት አዲስ ፈቃድ እና የፈቃድ እድሳት ያገኙ የ6396 የውጭ አገር ዜጎች መረጃ በኮምፒዩተር ተይዞ ለጥቅም ለማዋል በሚቻልበት መልኩ ተጠናቅሯል፣
- የማህበራት ምዝገባ ሰራዎችን የሚሰራ ሶፍትዌር ቀዳሚ ስራ የሆነውን የpreliminary Investigation ስራ ተሠርቷል፣
- ለ11 ሴት ና 34 ወንድ በድምሩ ለ45 የመ/ቤቱ ሠራተኞች የPower Point ስልጠና ተሰጥቷል፣

- ለተጠቃሚዎች መድረስ ያለባቸው መረጃዎች ከመ/ቤቱ የስራ ክፍሎችና ከሁሉም የክልል ቢሮዎች ተሰብስበው በመ/ቤቱ ድህረ ገጽ ላይ  ንዲሠፍሩ ተደርጓል፡፡

## 2. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ፣

### ግብ 2.1. አዋጅ፣ ፖሊሲ፣ ደንብ  መመሪያ ዝግጅት፣

### ግብ 2.1.1 የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ማሻሻያ፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ቀደም ሲል በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካሎች ጋር ውይይት በማካሄድ በአዋጁ ማሻሻያ ላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመወያየት በማዳበርና በአማካሪ ቦርድ አቅርቦ በማስገምገም ረቂቁን የመጨረሻ መልክ በማስያዝ ለበላይ አካል ለማቅረብ ታቅዶ፡-  የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ማሻሻያ ለማዘጋጀት በዋነኛነት በመሰረ ዊ  የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ተለይተው የወጡትን እንዲሁም የክልል አካላትንና የአሠሪና ሠራተኛ ብሔራዊ ማኀበራት የአፈጻጸም ችግሮችን የተመለከቱ መረጃዎች በማሰባሰብና አንቀጾችን በመለየት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል አካላት በጋራ አውደ ጥናት ውይይትና ምክክር ከተደረገባቸው በኋላ ተለይተው ወጥተው በየደረጃው ቀጣይ ጥናትና ውይይት እንዲደረግባቸው ተወስኗል፡፡

***የዕቅዱ ፋይዳ፡- የአዋጁን ድንጋጌዎች ወቅታዊነት መፈተሽ፣***

### ግብ 2.1.2 ብሄራዊ የሙያ ደህንነት ፖሊሲ ማዘጋጀት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለፖሊሲው መነሻ ጽሑፍ በማዘጋጀትና ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ አካላት እንዲመለከቱና በአማካሪ ተደግፎ የፖሊሲውን ረቂቅ ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-
ብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲን በሀገር አቀፍ ደረጃ  ያለውን የሙያ ጤንነትና ደ ንነት አጠቃላይ ሁኔ  የሚያሳይ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ጉዳዩ የሚመለከ ቸው አካላት በተሳተፉበት የምክክር አውደ ጥናት እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ ረቂቅ ፖሊሲውን ለማዘጋጀት የታቀደውን የውጭ አገር ባለሙያ ድጋፍ ማግኘት ባለመቻሉ ቀጣዩ ሥራ አልተከናወነም፣

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡-የሙያ ጤንነትና ደኅንነት ባህልን ማጎልበት፣***

### ግብ 2.1.3. ብሔራዊ የሥራ ስምሪት ፖሊሲ፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ቀደም ሲል የተዘጋጀውን የሥራ ሥምሪት ፖሊሲ ጥናት ሪፖርት ለማዳበርና ለውሳኔ ለማቅረብ ታቅዶ፡-

የጥናት ሪፖርቱን በመጀመሪያ በፌዴራል ደረጃ ጉዳዩ ከሚመለከ ቸው አካላት በተውጣጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች በመቀጠልም ከክልል ሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የተወጣጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች የተሳተፉባቸው ሁለት የምክክር ወርክሾፖች ተዘጋጅተው ሰነዱ እንዲዳብር ተደርጓል:: የፖሊሲ ፍሬም ወርክ አስይዞ ለማፀደቅ እንዲቻል ለባለድርሻ አካላት ለአስተያየት ተሰራጭቷል፡፡

*<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- የሥራ አጥነት ችግርን ለመከላከል የሚያስችል አቅጣጫ መቀየስ የሥራ ዕድል ማስፋፋያ*

### ግብ 2.1.4. ስለግል አገልግሎት የሥራ ሁኔታ የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ፣

ስለግል አገልግሎት የሥራ ሁኔታ የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ዙርያ በድሬዳዋ፣ በአዋሣ፣ በጅማ፣ በባህርዳር፣ በመቀሌና በአዳማ ጥናት በማካሄድ የጥናት ሪፖርት ማዘጋጀት፣ ማስገምገምና ረቂቅ ደንቡን ለማዘጋጀትና የመጨረሻ መልክ አስይዞ ለበላይ አካል ለማቅረብ ታቅዶ፡-

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቀጥር 377/96 አንቀጽ 3(ሐ) ላይ ስለ ግል አገልግሎት የስራ ሁኔ  የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ  ንደሚያወጣ በተደነገገው መሰረት ደንቡን ለማዳበር በተጠቀሱት ስድስት ከተሞች መረጃ በማሰባሰብና በመተንተን ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶና በአስተያየት ዳብሮ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

*<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- ስለግል አገልግሎት የሥራ ሁኔታ ደንብ ይዘጋጃል፣*

### ግብ 2.1.5. ለተሻሻለው የሥራና ሠራተኛ ማገናኛ አገልግሎት አዋጅ የአፈፃፀም መመሪያ ማዘጋጀት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር 104/90 የአፈፃፀም መመሪያ ረቂቅ ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-

በአገር ውስጥ ቀደም ብለው የተሰሩና የሌሎች አገሮች ልምድ /ሕንድ/ የሚያሳዩ ዶክመንቶች ተሰባስበው ተፈትሸዋል፡፡ ቀጣዩ ሥራና ሠራተኛ ማገናኛ አዋጅ የማሻሻል ስራ ዘግይቶ በመውጣቱ ተፈጻሚ አልተደረገም፡፡

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- የሥራ ዕድል ለማስገኘት ምቹ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣***

### ግብ 2.1.6. ብሔራዊ የሙያ በሽታ ዝርዝር ጋይድላይን ማዘጋጀት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በአማራ፣ በአፋር፣ በትግራይ፣ በአዲስ አበባ መረጃ በማሰባሰብ ብሔራዊ የሙያ በሽታ ዝርዝር ጋይድላይን ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-

በናሙናነት ከተመረጡ 18 ድርጅቶች፣ ከአምስት የሕክምና ቦርዶች፣ ከስድስት የክልል ቢሮዎች መረጃ ተሰብስቦና ተጠናቅሮ ብሔራዊ የሙያ በሽታ ዝርዝርን የተመለከተ ረቂቅ ጋይድላይን ተዘጋጅቷል፡፡

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- በሙያ በሽታ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ጋይድላይን ዝግጅት፣***

### ግብ 2.1.7 ኢንሹራንስ መግባት የሚገባቸውን ድርጅቶች መለያ መመሪያ ዝግጅት ጥናት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ፣ በድሬዳዋ፣ በሐረሪ፣ በአፋርና በአዲስ አበባ ከሚገኙ ድርጅቶች መረጃ በማሰባሰብ መመሪያውን ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-

በናሙና ደረጃ ከብረታ ብረት፣ ከግንባታ፣ ከማዕድንና ኃይል ማመንጫ፣ ከእርሻ፣ ከጨርቃጨርቅና ከአገልግሎት ኢንዱስትሪ ዘርፎች በናሙናነት ከተመረጡ 27 ድርጅቶችና ሶስት የኢንሹራንስ ኩባኒያዎች መረጃ ተሰብስቦ ተተነትኖና ተጠንቅሮ የጥናቱ ሪፖርት ተዘጋጅቶ በአስተያየት እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ ፡

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- የሥራ ሁኔታዎችን የሙያ ደኅንነትን ለማስጠበቅ ምቹ ሁኔታ ፣***

### ግብ 2.1.8 የለማጅ ሠራተኞች የሥራ ውል በማዘጋጀት ወደ ተግባር ማሸጋገር፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ቀደም ሲል የተዘጋጁ ውሎችን በመፈተሽ ጉድለታቸውን በመለየት ውሉን በማዘጋጀትና የመጨረሻ መልክ በማስያዝና በአስተያየት ወደ ተግባር ለማሸጋገር ታቅዶ፡-

በዕቅዱ መሠረት ቀደም ሲል የተዘጋጁ ውሎችን በመፈተሽ አዲስ የለማጅ ሠራተኛ የሥራ ውል ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት በአስተያየት ዳብሮ የመጨረሻ መልክ ይዞ ተዘጋጅቷል፡፡

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- ለለማጅ ሠራተኞች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት፣***

**ግብ 2.1.9 በሴቶችና ወጣቶች የሥራ ሁኔታዎች መመሪያ ፍተሻ ጥናት፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከተመረጡ ክልሎች ከሚገኙ የተለያዩ ድርጅቶች መረጃ በማሰባሰብ ሪፖርት ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-

በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በአማራ፣ በአፋር እና በደቡብ ከተመረጡ 29 ድርጅቶች የሴቶችና ወጣቶች መመሪያ አፈፃፀም መረጃ ተሰብስቦና ተጠንቅሮ ሪፖርት ቀርቦ በአስተያየት እንዲዳብር ተደርጓል፡፡

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡-የአፈፃፀም ግቦችን በመለየት ወጣቶችና ሴቶች በስራ ሁኔታዎቻቸዉ ዙሪያ መፍትሔ ለማስቀመጥ፣***

**ግብ 2.2. የሥራ ትብብርና ማኀበራዊ ውይይት ጥናት፣ ሥልጠናና ትምህርታዊ ጽሑፎች፣**

**ግብ 2.2.1 በአሠሪና ሠራተኛ መብትና ግዴታዎች ላይ እና የሁለትዮሽ አሠራርን ለማስረጽ የተሰጠ ስልጠና ፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በአሠሪና ሠራተኛ መብትና ግዴታዎች ላይ ለ45 ተሳታፊዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ፡-

ለ62 /3 ሴቶች እና 59 ወንዶች/ ተሳፊዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ የሥልጠናው ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡

**ግብ 2.2.3 *የአሠሪና ሠራተኛ አስተዳደር ስልጠና አሰጣጥ methdology ፣***

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለ50 ተሳታፊዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ፡-

ከፌደራል መ/ቤቱና ከክልል ቢሮዎች ለተውጣጡ 60 ባለሙያዎች /49 ወንድና 11 ሴት/ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

**ግብ 2.2.4. የኤች.አይ.ቪ./ኤድስን በሥራ ቦታ ለመከላከል፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሥራ ቦታ ጋይድላይን ላይ ለ30 የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ፡-

ለ3 ሴትና 20 ወንድ በአጠቃላይ ለ23 የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷል። የሥልጠናው አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

## ግብ 2.2.5. በሙያ ደህንነትና ጤንነት ሥራ አካባቢ ጥበቃ፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለሙያ ደኅንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ አባላት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ፡-

በአዲስ አበባ ለሚገኙና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ለ22 ወንድና እና 1 ሴት በአጠቃላይ ለ23 ሰልጣኞች ተሰጥቷል። የሥልጠናውም ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

## ግብ 2.2.6. የሕፃናት ጉልበት ሥራ ቁጥጥርን በተመለከተ፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሥራና ቁጥጥርን በተመለከተ በሕፃናት ጉልበት የምክክር አውደ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ፡-

የችግሩን ስፋትና ችግሩን በማስወገድ ረገድ ያሉትን ክፍተቶች ንዲሁም ያሉትን መልካም አጋጣሚዎች የሚያሳይ ጥናት ከተካሄደና ሪፖርት ከተዘጋጀ በ ላ በሪፖርቱ ላይ የተመሰረተ ችግሩን በሀገር አቀፍ ደረጃ በቅንጅትና በተደራጀ መንገድ ለመከላከል የሚያስችል ብሔራዊ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ መከላከያና መቆጣጠሪያ መርሃ ግብር /NPA/ ለማዘጋጀት የምክክር አውደ ጥናት ተካሂዶ በተገኘው ግብዓት መሠረት ረቂቅ የድርጊት መርሃ ግብሩ ተዘጋጅቶ አውደ ጥናቱ ተካሂዷል። ከዚሁ በተጨማሪም የሕፃናት ጉልበት ሥራን በተመለከተ ከተለያዩ የሜዲያ ድርጅቶች ለተውጣጡ 62 /13 ሴቶች እና 49 ወንዶች/ ተሳታፊዎች በዜና ዘገባና በሪፖርቲንግ ላይ ትምህርት ተሰጥቷል።

## ግብ 2.2.7. በሥራ ቦታ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ ማዕቀፍ፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ ማዕቀፍን ለማስተዋወቅ ሴሚናር ለማካሄድ ታቅዶ፡-

በሆስትዮሽ ደረጃ የተዘጋጀው የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በስራ ቦ መከ ተያና መቆጣጠሪያ በመንግስት/ሠ.ማ.ጉ.ሚ/ር/፣በአሠሪና በሠራተኛ ወገኖች ደረጃ በኦፊሴል የፊርማ ስነ ስርዓት በይፋ ወደ ስራ ንዲገባ ተደርጓል፡፡ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ ወደ ተግባር ለማሸጋገር በፖሊሲ ማዕቀፉ ላይ 28 /3 ሴትና 25 ወንድ/ የፌዴራልና የክልል አካላት የተሳተፉበት የማስተዋወቂያ ዓውደ ጥናት ተካሂዶ ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል፡፡

**ግብ 2.2.8. በተመረጡ 3 ክልሎች ለሚገኙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የተካሄደ የሥልጠና ፍላጎት፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በመንግሥት ልማት ድርጅቶች /በድሬዳዋ፣ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ/ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ፡-

የስልጠና ፍላጎት ለመለየት የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ መረጃ ተሰባስቦ የጥናት ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡

**ግብ 2.3.1. ስለግል የግልግል ዳኝነት አመሠራረትና አካሄድ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ማኅበራትን አደረጃጀትና ማኅበራዊ ምክክር፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ስለግልግል ዳኝነት አመሠራረትና አካሄድ ትምህርታዊ ጽሑፍ በማዘጋጀት ለክልሎች ለማከፋፈል ታቅዶ፡-

ትምህርታዊ ጽሑፉ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተሰራጭቷል፡፡

**2.3.3. በሥራ ሥምሪትና በሥራ ገበያ መረጃ አሰባሰብ አቅም ግንባታ፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በዘመናዊ የስራ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥና የስራ ገበያ መረጃ አያያዝና አሰባሰብ ላይ ለክልል ቢሮ የስራ ስምሪት ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ፡-

ለክልል የሥራ ሥምሪት ባለሙያዎች እንዲሁም 137 (64 ሴቶች እና 73 ወንዶች) ሥልጠና ተሠጥቷል፡፡ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡

**የዕቅዱ ፋይዳ ግንዛቤን ማዳበርና የማስፈፀም አቅም ማጎልበት፣**

**ግብ 2.3.3.2. ከአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ጋር በየሁለት ወሩ የምክክር መድረክ ለማዘጋጀትና ስላለው ሁኔታ ለመወያየት ታቅዶ፡-

በኩዌትና በሳውዲ አረቢያ ስላሉ ዜጎች ሁኔታ፣ በሕገወጥ ከሀገር ስለሚወጡ ዜጐች፣ ስለተጓዦች የህክምና ምርመራ ጉዳይ እና በአጠቃላይ በአዋጅ 104/90 አፈፃፀም ዙሪያ ውይይት ተካሂዷል።

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- የግል ሥራና ሠራተኛ አገልግሎት ችግሮችን ደረጃ በደረጃ መፍታት፣***

## ግብ 2.3.3.3 በአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዋጅ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በአዲስ መልክ በሚዘጋጀው የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዋጅ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-

አዋጁን የማሻሻል ሥራ ዘግይቶ በመውጣቱ ተፈጻሚ አልተደረገም።

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- በአዋጆቹ ላይ ግንዛቤ ማሳደግ፣***

## ግብ 2.3.4. ማኅበራትን፣ ኅብረት ስምምነትንና የሥራ ክርክርን አስመልክቶ ለሚቀርቡ ችግሮች ወቅታዊ መፍትሔ መስጠት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመወያየትና በውይይቱ ወቅት የተጠቆሙ ሃሳቦች ተግባራዊ ስለሚሆኑበት ስትራተጂ ለመንደፍ ታቅዶ ማኅበራትን፣ ኅብረት ስምምነትንና የሥራ ክርክርን አስመልክቶ ለሚቀርቡ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት፣ ችግሮችን የማሰባሰብ ሥራ የተከናወነ ሲሆን ለችግሮቹ መፍትሔ አመላካች አቅጣጫ ተቀይሷል።

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- የሚኒስቴር መ/ቤቱን አገልግሎቶች ማሳወቅ፣***

## ግብ 2.3.6 የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርዶች ባልተጠናከሩባቸዉ ክልሎች እንዲጠናከሩ ማድረግ፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶች ባልተጠናከሩባቸዉ ጋምቤላና አፋር ክልሎች ቦርዶቹ እንዲጠናከሩ ታቅዶ፡-

ከአፋርና ከጋምቤላ ብሔራዊ ክልሎች በመሰብሰብና በማጠናከር ሪፖርት ለማዘጋጀትና ለውሳኔ በማቅረብ ቦርዶቹ እንዲጠናከሩ መረጃ በማሰባሰብ ከሚመለከ ቸው የክልል አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ወሳኝ ቦርዶቹ ወደስራ ንዲገቡ ተደርጓል።

**ግብ 2.3.7 የሶስትዮሽ የምክክር መድረክ የአማካሪ ቦርድን ማጠናከር፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ቦርዱ በመደበኛነት በመሰብሰብ ባለፉት ዓመታት ስለተከናወኑ ሥራዎች የግምገማ ሪፖርት አጽድቋል። ከዚሁ በተጨማሪም በአንዳንድ ድርጅቶች የማነጅመንት አባላትና የሠራተኛ ማህበራት የሥራ አመራር አካላት መካከል በተፈጠረው አለመስማማት በተከሰቱ ችግሮች ላይ ተወያይቶ መፍትሔ አስቀምጧል።

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>:- የሶስትዮሽ አሠራርን ለማጎልበት ፣***

**ግብ 2.3.8 ለሥራ ወደ ውጪ አገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን የመረጃና የምክር አገልግሎት መስጠት፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለስራ ወደውጭ ሀገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን አጠቃላይ የመረጃና የምክር አገልግሎት በመስጠት ረገድ ለ21269 (3875 ወንዶች እና 17394 ሴቶች) ስለህጋዊነትና ህገወጥነት፣ ስለጤና፣ ስለሥነልቦና፣ ስለህጋዊና ህገወጥ ምልመላ መንገዶች፣ ስለገንዘብ አያያዝ፣ በሚሄዱበት አገር ስለሚያጋጥሙ የባህል ግጭቶችና መፍትሔዎቻቸው፣ ስለተቀባይ ሀገር ሃይማኖትና መደረግ ስላለባቸዉና መደረግ ስለሌለባቸው ጉዳዮች ወ.ዘ.ተ. በምስል የታገዘ ገለፃ ተሰጥቷል።

***የዕቅዱ ፋይዳ:- ለስራ ወደውጭ የሚሄዱ ዜጎችን ስለሚሄዱበት ሀገርና የስራ ሁኔታ ገለፃ በመስጠት ማሳወቅ፣***

**ግብ 2.4. የሥራ ሁኔታ ጥበቃ (Labour Protection)**

**ግብ 2.4.1 በተመረጡ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥሮች ማካሄድ፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በተመረጡ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ውስጥ መከታተያ ቁጥጥሮችን ለማካሄድ ታቅዶ:-

ቁጥጥር የሚካሄድባቸውን ድርጅቶች በመለየት በ16 ድርጅቶች ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ፣ በ8 ድርጅቶች የመከ ያ ቁጥጥሮች ተካሂደዋል፡፡ የቁጥጥር ሪፖርትም ተዘጋጅቶ ለድርጅቶቹ እንዲደርሳቸዉ ተደርጓል፡፡

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- የስራ ሁኔታዎች ቁጥጥር በማድረግ አፈፃፀምን መከታተል፣***

**ግብ 2.4.2 የሙያ ደህንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢዎች አፈፃፀም የቁጥጥር ፎርማቶችን /ቼክሊስቶችን/ ማዘጋጀት፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሙያ ደኅንነት ጤንነትና የሥራ አካባቢ ጥበቃ መመሪያ ለመፈተሽ ታቅዶ፡-

በእርሻና በግንባታ የኢንዱስትሪ ዘርፎች በሙያ ጤንነትና ደህንነት አፈፃፀም ላይ በጥናት ላይ የተመረኮዙ ሁለት ዝርዝር ቼክሊስቶች ተዘጋጅተው በአስተያየት እንዲዳብሩ ተደርጓል፡፡

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡-አፈፃፀምን ለመከታተል የሚያስችል ፎርማቶችን ማዘጋጀት፣***

**ግብ 2.5 የሥራ ገበያ መረጃ ማዘጋጀት፣ መሰብሰብና የሥራ ሥምሪት አገልግሎት መስጠት፣**

**ግብ 2.5.1. ወቅታዊ የሥራ ገበያ መረጃ ከክልሎች መሰብሰብና መተንተን፣ የሥራ ገበያ ሪፖርት ማዘጋጀትና የመረጃ ክምችት መፍጠር፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የ2002 በጀት ዓመት የስራ ገበያ መረጃ ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-

ለመረጃ ማሰባሰቢያ የሚረዱ ፎርማቶችን በማዘጋጀት ለክልሎች የሥራ ፈላጊዎችን ቁጥር በትምህርት ደረጃ፣ በሙያ፣ በዕድሜ ወዘተ..ሪፖርት የተደረጉ ክፍት የሥራ ቦ ዎችንና የተቀጠሩ ሥራ ፈላጊዎችን የሚያሳይ መረጃ ተሰብስቦና ተተንትኖ የ2000 ዓ.ም የሥራ ገበያ መረጃ መጽሄት ተዘጋጅቷል፡፡

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- ወቅታዊ የሥራ ገበያ መረጃ ማሰባሰብና ለተጠቃሚው ማሰራጨት፣***

**ግብ 2.5.2. የሥራ ፈቃድ አገልግሎት መረጃ ክምችት መፍጠር፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በመንግሥት የስራ ሥምሪትና በግል ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ወደ ውጭ ለስራ የሄዱ ኢትዮጵያውያን መረጃ ለማከማቸት ታቅዶ፡-

ለሥራ ወደ ውጭ የሚሄዱ ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ በኤጀንሲዎች እና በግል 21269 /3875 ወንድና 17394 ሴት/ እና ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለሚሰሩ የውጭ አገር ዜጎች ለ5379 ( 4903 ወንድና 476 ሴቶች) አዲስ የሥራ ፈቃድ፣ለ7349 (6715 ወንድና 634 ሴት) እድሳት እና ሥራቸውን ለጨረሱ 4090 (3777 ወንድና 313 ሴት/ የውጭ ዜጎች ክሊራንስ የተሰጣቸው በአጠቃላይ 16818 የውጭ አገር ዜጎች መረጃ ተሰባስቦ ታይቷል፡፡

*<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- የስራ ስምሪት የመረጃ ማሰባሰብና ማደራጀት ፣*

## ግብ 2.5.3. ቀልጣፋ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት መስጠት

## ግብ 2.5.3.1. በእርሻ ሥራ ላይ ወቅታዊ የጉልበት ሠራተኛ እጥረት ያለባቸዉን ክልሎች ማጥናት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በእርሻ ስራ ላይ ተሰማርተው ወቅታዊ የጉልበት ሠራተኛ እጥረት ያለባቸውን ክልሎች ለማጥናት ታቅዶ፡-

በአማራ ክልል፣ በመተማና በቤንሻጉል ክልል በእርሻ ሥራ የተሰማሩትን ባለሐብቶች ሥራና ሠራተኛ በማገናኘት ረገድ ያለባቸውን ችግሮች ጥናት ተካሂዶ የጥናት ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላትና ለክልሎቹ ተልኳል፡፡

## ግብ 2.5.3.2. የሥራ ፈቃድ አገልግሎት፣

በበጀት ዓመት ውስጥ ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ዕድሳትና ክሊራንስ፣ ወደውጭ ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ደግሞ የስራ ውል ለማፅደቅ ታቅዶ፡-

ለሥራ ወደ ውጭ የሚሄዱ ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ በኤጀንሲዎች በኩል 14891 (1663 ወንድና 13338 ሴት) ሠራተኞች የሥራ ውላቸው በመሥሪያ ቤታችን በኩል ፀድቆ እንዲመዘገቡ የተደረገ ሲሆን በግል ጥረታቸው ሥራ በማግኘት 6378 (2212 ወንድና 4166 ሴት) አመልካቾች ወደ ተለያዩ አገሮች ለመሄድ የሥራ ውላቸውን ያቀረቡ አስፈላጊው ፎርማሊቲ ተሟልቶ ተመዝግበዋል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለ21269 ዜጎች የስራ ፈቃድ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለሚሰሩ የውጭ አገር ዜጎች ለ5379 (4903 ወንድና 476 ሴት) አዲስ የሥራ ፈቃድ፣ለ7349 (6715 ወንድና 634 ሴት) እድሳት እና ሥራቸውን ለጨረሱ ለ4090 (3777 ወንድና 313 ሴት) የክሊራንስ በአጠቃላይ ለ16818 የውጭ ዜጎች አዲስ የሥራ

ፈቃድ፣እድሳትና የክሊራንስ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 104/90 መሠረት ዜጎችን ከኢትዮጵያ ውጭ በሥራ ለማሰማራት እንዲችሉ ለ20 ኤጀንሲዎችና በአገር ውስጥ ሥራና ሠራተኛን ለማገናኘት ፈቃድ ለጠየቁ 9 ኤጀንሲዎች የሥራ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን ለ28 ኤጀንሲዎች የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ተከናውኗል፡፡

## ግብ 2.5.3.3. የውጪ አገር ዜጎችን የሥራ ፈቃድ አፈፃፀም ክትትል ማድረግ፣

በበጀት ዓመት ውስጥ የውጭ አገር ዜጎች የስራ ፈቃድ አፈፃፀም ክትትል ለማድረግ ታቅዶ፡- የክልል ቢሮዎች በየክልላቸው ተመድበው የሚሰሩትን የውጭ አገር ዜጐች የሥራ ፈቃድ ሁኔታ በኢንስፔክተሮቻቸው ቁጥጥርና ክትትል እንዲያደርጉ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃ ተሰራጭቶላቸዋል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ በተለያዩ ድርጅቶች ጥያቄ አማካኝነት አገር ውስጥ ገብተው የሥራ ፈቃድ ካገኙ በኂላ ባልተፈቀደላቸው የሥራ አካባቢ በድብቅ እየሰሩ መሆናቸውና አድራሻቸውን ማግኘት እንዳልቻሉ ላመለከቱት ጥቆማ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኢንስፔክተሮች ቁጥጥር ተደርጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

## ግብ 2.5.3.4. በአገር አቀፍ ደረጃ የሥራ ሥምሪት የሚሰጡ ኤጀንሲዎችን ፕሮፋይል ማዘጋጀት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በ73 ሕጋዊ ኤጀንሲዎች ላይ የቁጥጥር ስራ ለማካሄድ ታቅዶ፡- በአገር አቀፍ ደረጃ የሥራ ሥምሪት የሚሰጡ ኤጀንሲዎችን ፕሮፋይል፣ የኤጀንሲዎቹን ዝርዝር አድራሻ የያዘ ረቂቅ ፕሮፋይል ተዘጋጅቷል፡፡

## ግብ 2.5.3.5. በ73 ፈቃድ ያላቸው የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ላይ የቁጥጥርና የክትትል ሥራ ማካሄድና ሪፖርት ማዘጋጀት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሶስት የተለያዩ የሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማቶች በማዘጋጀት ከ78 ኤጀንሲዎች ሪፖርት ተሰብስቧል፡፡ ንዲሁም በግል ጥረ ቸዉ ሥራ አግኝተው በሚ/ር መ/ቤቱ በኩልና በተለያዩ አሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች አማካኝነት ለሥራ ወደ ውጭ ሄደው በደል ደርሶብናል በሚል አቤቱ ለሚያቀርቡ ዜጎች ከኤምባሲዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ችግሮቻቸዉን ለመቅረፍ ተሞክሯል፡፡

*<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- ቀልጣፋ በስራ ስምሪት አገልግሎት መስጠትና በአፈፃፀሙ ላይ ክትትል ማድረግ፣*

## 3. የማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ

**ግብ 3.1 ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ወደ ተግባር የማሸጋገር አቅምን ማጎልበት፣**

**ግብ 3.1.1. የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ የድርጊት መርሐ ግብር አፈፃፀም የቅንጅት መድረክ /Council / በ7 ክልሎች ማቋቋም፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከክልሉ ሠ.ማ.ጉ ቢሮች ጋር በመነጋገር አግባብ ያላቸውን ተሳታፊዎችን በመለየትና የቅድመ ዝግጅት ሥራውን በማጠናቀቅ በፌደራል፣ በትግራይ፣ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላና በቤንሻጉል የአካል ጉዳተኞች ፎረሙን ለማቋቋም ታቅዶ በትግራይ፣ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላና በቤንሻጉል የአካል ጉዳተኞች ካውንስል ተቋቁሟል።

**ግብ 3.1.2 የአረጋውያን የድርጊት መርሐግብር አስፈጻሚ ፎረሞች ግምገማ፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የአረጋውያን የድርጊት መርሃ ግብር አስፈፃሚ ፎረሞች ለማቋቋም ታቅዶ፡-

በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባ፣ በቤንሻጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ፎረሙ ተቋቁሟል። እንዲሁም በሐረሪና በድሬደዋ የአፈፃፀም ግምገማ ተካሂዶ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

**ግብ 3.1.3 የተጠናቀቀ የቤተሰብ የድርጊት መርሃግብር፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የቤተሰብ የድርጊት መርሐ ግብር ለማጠናቀቅ ታቅዶ፡-

ረቂቅ የቤተሰብ የድርጊት መርሐግብር በመ/ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ እንዲተች በማድረግ የቀረቡ አስተያየቶችን በማካተት ለክልል ሠ.ማ.ጉ ቢሮዎች በመላክ በረቂቅ ደረጃ የማዘጋጀቱ ስራ ተጠናቆ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የሚመክሩበት ዓውደ ጥናት ተዘጋጅቶ በረቂቁ ላይ የማዳበሪያ አስተያየት ተሰባስቧል።

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን የድርጊት መርሐ ግብር ማስፈፀሚያ ፎረም ማቋቋምና ማጠናከርና የቤተሰብ የድርጊት መርሐ ግብር ሰነድ ማዘጋጀት፣***

**ግብ 3.2 በማኅበራዊ ደኅንነት ዙሪያ የተፈጠረ የግንዛቤ መድረክ እና የተሰጠ ሥልጠና ፣**

**ግብ 3.2.1 የአካል ጉዳተኞች የሥራ ሥምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000 የማስተዋወቅን በተመለከተ፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ አዋጅ ቁጥር 568/2000 ለማስተዋወቅ ታቅዶ፡-

(19 ሴቶች እና 70 ወንዶች) በድምሩ 89 ተሳታፊዎች በተገኙበት በአዲስ አበባና በናዝሬት ከተማ የግንዛቤ ማዳበሪያ ዓውደ ጥናቶች ተካሂዶ የአውደ ጥናቱ ሪፖርቶች ተዘጋጅተዋል።

**ግብ 3.2.2 ለ30 ለክልል ሠ.ማ.ጉ ቢሮዎች፣ ለአካል ጉዳተኞች ማኀበራት፣ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች በፕሮጀክት ዝግጅት አፈፃፀም እና ግምገማ ስልጠና፣**

በበጀት ዓመቱ ተሳታፊዎችን በመለየት ሥልጠናው እንዲካሄድ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ፡-

የሥልጠና ተሳታፊዎችን በመለየት ለ27 ሰዎች (5 ሴቶች እና 22 ወንዶች) ሥልጠ ተሰጥቷል።

**ግብ 3.2.3 የጋብቻና ቤተሰብ አመራርና ምክር ማኑዋል ላይ ለባለሙያዎች ሥልጠና፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሥልጠና ማቴሪያል በማዘጋጀትና የቅድመ ዝግጅት ሥራውን በማጠናቀቅ ከሶስት ብሔራዊ ክልሎች ለመጡ ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል።

**የዕቅዱ ፋይዳ፡- ግንዛቤ ማሳደግና የባለሙያዎች አቅም መገንባት፣**

**ግብ 3.3. የማኀበራዊ ልማት ፈንድ ረቂቅ ሰነድ ማዘጋጀት፣**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የኀብረተሰብ ክፍሎችን ለማቋቋም የማኀበራዊ ልማት ፈንድ ረቂቅ የሕግ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የኀብረተሰብ ክፍሎችን ለመርዳትና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል የማኀበራዊ ድጋፍ ፈንድ ማቋቋሚያ ጥናት በኮንሰልታንት ለማስጠናት ከበጎ ፈቃደኛ ተቋም በተገኘው ድጋፍ የፕሮጀክት ዶክመንትና የጥናቱ ሥራ ተጀምሯል።

*የዕቅዱ ፋይዳ፡- ለውሳኔ መሠረት የሚሆን የጥናት ሰነድ ማዘጋጀት፣*

## ግብ 3.4. ብሔራዊ የልመና ማስወገጃ ሥራ ተቋማዊ በሆነ መንገድ በዘላቂነት ለማካሄድ የሚያስችል በፌዴራልና በክልል ተቋማዊ አሠራርና አቅም መፍጠር፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብሔራዊ የልመና ማስወገጃ ስራ ተቋማዊ አሠራርና አቅም ለመፍጠር ታቅዶ፡-

በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብና በድሬዳዋ ክልሎች የልመና መልሶ ማቋቋሚያ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ድጋፍ ለመስጠት፣ ሁለት የጋራ የምክክር መድረኮችን ለመፍጠር እና የመልሶ ማቋቋሚያ ፕሮግራሙን በማስተባበር በመከታተል ድጋፍ በመስጠት የአፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀት የልመና መልሶ ማቋቋሚያ ተግባራትን የሚያስተባብሩ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል፡፡ በአዲስ አበባ አስተዳደር ኮሚቴውን ለማቋቋም የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ባለሃብቶች የተካፈሉበት ሁለት የምክክርና የገቢ ማስገኛ መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ የመልሶ ማቋቋሚያ ፕሮግራሙን በማስተባበርና በመከታተል የአፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

**<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡- ተቋማዊ አሰራር እና የማስፈጸም አቅም ይዳብራል፣**

## ግብ 3.5. ብሔራዊ የልመና ማስወገጃ ዘመቻ ላይ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥራ ማከናወን፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ የልመና መልሶ ማቋቋሚያ ኮሚቴዎችን ለማቋቋምና የልመናና አስከፊነት ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ፡-

በሬዲዮና በቴሌቪዥን የግንዛቤ ትምህርት ተሰጥቷል ፡፡ በልመና የተሰማሩ ዜጎችን መልሶ የማቋቋም ሥራን አስመልክቶ በፌደራል ደረጃ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ተሰጥተዋል፡፡በአራቱም የሐይማኖት ተቋማት መሪዎች በምጽዋትና በዘካት አሰጣጥና በመልሶ ማቋቋም ሥራ ላይ የምክክርና የግንዛቤ ማዳበሪያ መድረክ ተካሂዷል፡፡ በቴሌቶን መራዘም ምክንያት የግንዛቤ ማዳበሪያ መድረኮችን የማካሄድና ትምህርታዊ ድራማ ማዘጋጀት አልተቻለም፡፡

## ግብ 4 በሚ/ር መ/ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መስራት፣

### ግብ 4.1. ሴቶችን በሚመለከት በወጡ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ስምምነቶችና መርሐ ግብር ላይ የተከናወኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ 181(119 ሴቶችና 62 ወንዶች) የመ/ቤቱ ሰራተኞች ሴቶችን በሚመለከት በወጡ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ስምምነቶችና መርሐግብሮች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ተከናውኗል፡፡

### ግብ 4.2 ስርዓተ ፆታ ላይ ሥልጠና መስጠት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሥልጠና ፅሁፍ በማዘጋጀት ለ30/15 ሴቶች እና 15 ወንዶች/ ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠትና የስልጠናውን ሪፖርት ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-
የቅድመ ዝግጅት ሥራው የተጠናቀቀ ቢሆንም ተስፋ የተደረገበት የማስፈጸሚያ በጀት ባለመገኘቱ ሥልጠናው አልተሰጠም፡፡

### ግብ 4.3 ሴቶችን የተመለከተ መረጃ ማሰባሰብ፣ ማደራጀትና ሪፖርት አዘጋጅቶ ለተጠቃሚ ማሰራጨት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንዴት ሥር ከሚገኙ በልማት ድርጅቶች ውስጥ የሴት ሠራተኞችን ሁኔታ የሚያሳይ ሁለተኛ ደረጃ መረጃ ተሰባስቧል፡፡

### ግብ 4.4 ስርዓተ ፆታን በዕቅድና በፕሮግራም ለማካተት ረቂቅ ጋይድ ላይን ማዘጋጀት፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለቢጋር ዝግጅት ጽሁፎችን በማገናዘብ ቢጋሩን በማዘጋጀት ረቂቅ ጋይድላይኑን ለማዘጋጀት ታቅዶ፡-
ጋይድላኑን ለማዘጋጀት የሚያስችል ቢጋር በማዘጋጀት እና መረጃዎችን በማሰባሰብ ለመነሻ የሚያገለግል ጽሁፍ በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡

### ግብ 4.5 ማርች 8 የሴቶች ዓለም ዓቀፍ በዓልን ማክበር፣

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ማርች 8 ዓለም አቀፍ በዓልን ለማክበር ታቅዶ፡-

በዕቅዱ መሠረት ዕለቱ የሴቶች ሁለተናዊ ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት እውን ይሆናል በሚል አገራዊ መሪ ሀሳብ ዙሪያ ቀኑ በመ/ቤቱ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተከብሯል፡፡

***<u>የዕቅዱ ፋይዳ</u>፡-*** **ግንዛቤ የማሳደግና መረጃን አሰባስቦ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣**

## <u>በበጀት ዓመቱ ውስጥ በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች</u>፣

### *ሀ/ <u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>፣*

- ብቃት ያለው የሰው ኃይል እጥረት፣
- ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ትብብር አነስተኛ መሆን፣

### *ለ/ <u>የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች</u>፣*

- ከገበያ ለመሙላት ጥረት የማድረግ እንዲሠሩ ተደርጓል፣
- በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውስጥ የቅንጅትና የትብብር አሠራር ተጠናክሮ የሚሄድበት ጥናት ተካቷል፣

# አ ባ ሪ

# በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሐምሌ 1/2000 - ሰኔ 30/2001 ዓ.ም ድረስ ያለው የሰው ይል ሁኔ

| የትምህርት ደረጃ | ጾ | በመዋቅር የተፈቀደ | ሰኔ 30/2000 መጨረሻ የነበረ | የሰው ይል | | | | | | | | | | በሥራ ላይ ያሉ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የተቀነሰ | | | | | | የተጨመረ | | | | |
| | | | | በዝውውር | በስንብት | በጡረ | በሞት | በሌላ | ድምር | በቅጥር | በዝውውር | በሌላ | ድምር | |
| (1) | (2) | (3) | (4) | (5) | (6) | (7) | (8) | (9) | (10) | (11) | (12) | (13) | (14) | 15=(4-10)+14 |
| ዲግሪ | ወ | | 38 | | 3 | | | 1 | 4 | 3 | 4 | | 7 | 41 |
| | ሴ | | 13 | | 3 | | | - | 3 | 2 | - | | 2 | 12 |
| | ድ | | 51 | | 6 | | | 1 | 7 | 5 | 4 | | 9 | 53 |
| ዲኘሎማ 35 | ወ | | 17 | | | | 1 | 1 | 2 | | | | | 15 |
| | ሴ | | 20 | | | | - | - | - | | | | | 20 |
| | ድ | | 37 | | | | 1 | 1 | 2 | | | | | 35 |
| ዩኒቨርስቲ ያላጠናቀቁ | ወ | | 1 | | | 1 | 1 | | 1 | | | | | - |
| | ሴ | | - | | | - | - | | - | | | | | - |
| | ድ | | 1 | | | 1 | 1 | | 1 | | | | | - |
| የቴክኒክና ሙያ ት/ቤት ዲኘሎማ | ወ | | 9 | | - | | | | 1 | | | | | 8 |
| | ሴ | | 29 | | 2 | | | | 2 | | | | | 27 |
| | ድ | | 38 | | 2 | | | | 3 | | | | | 35 |
| 9 - 12 | ወ | | 23 | | 1 | | | | 1 | | | | | 22 |
| | ሴ | | 52 | | 1 | | | | 1 | | | | | 51 |
| | ድ | | 75 | | 2 | | | | 2 | | | | | 73 |
| 1 - 8 | ወ | | 29 | | | | | | | | | | | 29 |
| | ሴ | | 34 | | | | | | | | | | | 34 |
| | ድ | | 63 | | | | | | | | | | | 63 |
| ማንበብና መጻፍ | ወ | | 22 | | | 2 | | - | 2 | | | | | 22 |
| | ሴ | | 23 | | | 3 | | 1 | 4 | | | | | 18 |
| | ድ | | 45 | | | 5 | | 1 | 6 | | | | | 40 |
| **ጠቅላላ ድምር** | ወ | | 140 | | 4 | 3 | 2 | 2 | 11 | 3 | 4 | | 7 | 137 |
| | ሴ | | 171 | | 6 | 3 | - | 1 | 10 | 2 | - | | 2 | 162 |
| | ድ | 386 | 311 | | 10 | 6 | 2 | 3 | 21 | 5 | 4 | | 9 | 299 |

# ከሐምሌ 1/2000 እስከ ሰኔ 30/2001 ዓ.ም የመደበኛ በጀት አጠቃቀም ሪፖርት

| የወጪ መደብ | የወጪ ርዕስ መግለጫ | ለ2001 የተፈቀደ በጀት | የአራተኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ | በአራተኛ ሩብ ዓመት ሥራ ላይ የዋለ በጀት | ክንውን በመቶኛ | የበጀት ዓመቱ ዕቅድ | በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ የዋለ በጀት | ክንውን በመቶኛ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ሥራ ላይ የዋለ በመቶኛ | የበጀት ዝውውር የተደረገ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6=5/4 | 7 | 8 | 9=8/7 | 10=(3-8)±11 | የበጀት ዝውር የተደረገ |
| 6111 | ለቋሚ ሠራተኞች ደመወዝ | 4,643,800 | 977,859.00 | 1,082,532.97 | 111 | 4,622,570.00 | 4,569,013.89 | 99 | 74,786.11 | |
| 6121 | ለቋሚ ሠራተኞች አበል | 89,200 | 19,499.10 | 18,049.10 | 93 | 82,346.40 | 79,596.40 | 97 | 9,603.60 | |
| 6116 | ለሠራተኛ የማደረጉ ክፍያዎች | | | | | | | | | |
| 6131 | ለቋሚ ሠራተኞች የሠራተኛ ጡረታ መዋጮ | 278,700 | 58,172.36 | 63,373.11 | 109 | 276,879.02 | 272,810.73 | 99 | 5,889.27 | |
| 6211 | ለደንብ ልብስ | 108,400 | 12,900.00 | 24,481.07 | 190 | 108,400.00 | 106,477.57 | 98 | 1,922.43 | |
| 6212 | ለአላቂ የቢሮ እቃዎች | 212,800 | 13,800.00 | 20,354.84 | 147 | 212,800.00 | 209,900.51 | 99 | 2,899.49 | |
| 6213 | ለህትመት | 118,000 | 35,000.00 | 61,125.85 | 175 | 118,000.00 | 100,336.450 | 85 | 17,663.55 | |
| 6214 | ለአላቂ የህክም ዕቃዎች | 2,000 | | | | 1,000.00 | | 0 | 2,000.00 | |
| 6215 | ለአላቂ የትምህርት እቃዎች | 11,700 | | 1,663.35 | | 11,700.00 | 6,767.95 | 58 | 4,932.05 | |
| 6217 | ለነዳጅ ቅባቶች | 306,100 | 49,300.00 | 76,162.41 | 154 | 336,100.00 | 335,858.68 | 100 | 241.32 | 30000.00 |
| 6218 | ለሌሎች አላቂ እቃዎች | 42,500 | 2,500.00 | 7,367.62 | 295 | 42,500.00 | 42,493.77 | 100 | 6.23 | |
| 6219 | ለተለያዩ መሳሪያዎችና መጽሃፍት | 1,000 | | | | 1,000.00 | | 0 | 1,000.00 | |
| 6231 | ለውሎ አበል | 669,300 | 128,800.00 | 199,510.45 | 155 | 452,900.00 | 268,997.90 | 59 | 310,302.10 | (90000.00) |
| 6232 | ለትራንስፖርት ክፍያ | 352,700 | 180,700.00 | 186,930.00 | 103 | 290,305.00 | 265,786.45 | 92 | 86,913.55 | |
| 6233 | ለመስተንግዶ | 19,400 | 4,900.00 | 2,160.50 | 44 | 19,400.00 | 17,058.18 | 88 | 2,341.82 | |
| 6241 | ለተሽከርካሪዎች ሌሎች መንገዣ እድሳት ጥገ | 204,900 | 61,900.00 | 23,759.13 | 38 | 244,900.00 | 217,852.81 | 89 | 27,047.19 | 40000.00 |
| 6243 | ለፕላንት፣ ለማሽነሪ ለመሣሪያ እድሳት እ ጥገ | 50,000.00 | 15,000 | 17,605.94 | 117 | 50,000 | 45,623.44 | 91 | 4,376.56 | |
| 6244 | ለህንጻ ቁሳቁስ ለተገጣጣሚ እድሳት ጥገ | 90,000.00 | 20,000 | 50,425.41 | 252 | 90,000 | 83,930.78 | 93 | 6,069.22 | |
| 6253 | ለማስታወቂያ | 163,600.00 | 28,600 | 34,589.50 | 121 | 127,600 | 114,409.90 | 90 | 13,190.10 | (36000.00) |
| 6254 | ኢንሹራንስ | 95,800.00 | 500 | 15,106.61 | 3,021 | 70,700 | 70,516.07 | 100 | 183.93 | (25100.00) |
| 6255 | ለጭነት | 12,000.00 | 3,000 | 5,020.56 | 167 | 12,000 | 11,846.06 | 99 | 153.94 | |
| 6256 | ለአገልግሎት ክፍያዎች | 48,100.00 | 5,100 | 26,200.26 | 514 | 48,100 | 35,815.83 | 74 | 12,284.17 | |
| 6257 | ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ | 72,600.00 | 18,150 | 16,152.82 | 89 | 72,600 | 68,753.72 | 95 | 3,846.28 | |
| 6258 | ለቴሌኮሙኒከ ሽን አገልግሎት ክፍያ | 269,600.00 | 117,100 | 77,941.72 | 67 | 319,600 | 286,683.24 | 90 | 32,916.76 | 50000.00 |
| 6259 | ለውሃ፣ለፖስታ ለሌሎች አገልግሎት ክፍያዎች | 43,100.00 | 21,881 | 21,921.60 | 100 | 54,200 | 49,057.40 | 91 | 5,142.60 | 11100.00 |
| 6271 | ለሥልጠ አገልግሎት | 203,000.00 | 56,032 | 40,696.44 | 73 | 203,000 | 118,299.07 | 58 | 84,700.93 | |
| 6313 | ለቋሚ ንብረቶች | 73,800.00 | | 16,129.65 | | 73,800 | 35,670.85 | 48 | 38,129.15 | |
| 6314 | ለቋሚ ኤሌክተሮኒክስ ዕቃዎች መግዛ | 22,900.00 | | | | 22,900 | 7,365.10 | 32 | 15,534.90 | |
| 6412 | ለተቋማት፣ ለድርጅቶች፣ እርዳታ መዋጮ ድጎማ | 120,000.00 | 30,000 | 45,000.00 | 150 | 120,000 | 115,000.00 | 96 | 5,000.00 | |
| 6414 | ለአለም አቀፍ ድርጅቶች መዋጮ | 277,000.00 | 20,000 | | 0 | 297,000 | 296,098.59 | 100 | 901.41 | 20000.00 |
| 6417 | ለግለሰቦች እርዳታ እ ስጦታ | 800.00 | 200 | | 0 | 800 | | 0 | 800.00 | |
| ጠቅላላ ድምር | | 8,602,800.00 | 1,880,893.46 | 2,134,260.91 | 113 | 8,383,100 | 7,832,021.34 | 93 | 770,778.66 | 0.00 |

## *በበጀት ዓመቱ ውስጥ የበጀት አፈፃፀማቸዉ ዝቅተኛ ለሆኑ የወጪ አርዕስቶች የቀረበ ማብራሪያ*

### *6215. አላቂ የትምህርት ዕቃዎች*

- ለቤተ መጻሕፍት የሚሆኑ ልዩ ልዩ ለሥራ አጋዥ የሚሆኑ መጽሐፍቶች ለመግዛት ዕቅድ ተይዞ ከየሥራ ክፍሎች የሚያስፈልጉትን የመጻሕፍት ግዥ ዝርዝር ቢቀርብም በሀገር ውስጥ ገበያ ሊገኝ ባለመቻሉ ግዥው ሳይፈፀም በመቅረቱ፣

### *6231. ለውሎ አበል*

- በሀገራችንና በግብፅ መንግሥታት መካከል በማኅበራዊ ደኅንነት ልማት መስክ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ በተደረገው ስምምነት መሠረት በበላይ ኃላፊ የሚመራ የልዑካን ቡድን በውይይቱ ላይ ለመገኘት በዕቅድ ተይዞ የነበረው ስብሰባ (ጉዞው) በመቅረቱ ምክንያት ወጪ ሊቀንስ ችሏል፣
- የአፍሪካ ሌበር ኮምሽን ስብሰባ /በተመረጠ አገር/ ላይ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊና የልዑካን ቡድን ለመሳተፍ በዕቅድ ተይዞ የነበረው ስብሰባው በመቅረቱ ምክንያት ወጪው ዝቅ ብሎ ሊታይ ችሏል፣
- የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኅዳር 2001 ዓ.ም እና መጋቢት 2001 ዓ.ም ለሚደረገው የዓለም ሥራ ድርጅት የአስተዳደር አካል ስብሰባ ላይ ለመሣተፍ ዕቅድ ተይዞ ጉዞው በመቅረቱ ምክንያት ወጪው አንሶ ሊታይ ችሏ።

*6256.* በዚህ የበጀት ርዕስ የተያዘው በጀት ከዕቅዱ በታች ዝቅ ብሎ ሊታይ የቻለው ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የውጭ ጉዞ በመቅረቱ ምክንያት ወጪው ከዕቅዱ በታች አንሶ ሊታይ ችሏል።

*6271.* በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች በሲቪል ሠርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት በኩል በሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ሥልጠና ለመስጠት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ተቋሙ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የኘሮግራም ለውጥ በማድጉ ሥልጠናው ባለመሰጠቱ ወጪው አንሶ ሊታይ ችሏል።

## 6313. ለኘላንት ማሽነርና ለመሣሪያ ግዥ

- የቋሚ ዕቃዎች ለመግዛት በጋዜጣ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ ተወዳዳሪዎች ተመዝግበው ሠነድ ወስደው የተወዳደሩ ቢሆንም አሸናፊው ዕቃዎችን በውሉ መሠረት ሊያቀርብ ባለመቻሉ ያስያዘው ገንዘብ ወደ መንግሥት ካዝና ገቢ የተደረገ ሲሆን የተፈለገው ዕቃ በገበያ ላይ ለጊዜው ባለመገኘቱ ግዥ ሊፈፀም ባለመቻሉ፣

## 6314. የሕንፃ የቤት ዕቃ የቤት ውስጥ ተገጣጣሚዎች ግዥ፣

- የቋሚ ዕቃዎች ለመግዛት በጋዜጣ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ ተወዳዳሪዎች ተመዝግበው ሠነድ ወስደው የተወዳደሩ ቢሆንም አሸናፊው ዕቃዎችን በውሉ መሠረት ሊያቀርብ ባለመቻሉ ያስያዘው ገንዘብ ወደ መንግሥት ካዝና ገቢ የተደረገ ሲሆን የተፈለገው ዕቃ በገበያ ላይ ለጊዜው ባለመገኘቱ ግዥ ሊፈፀም ባለመቻሉ፣

6417. ከቀድሞ ኢትዮጵያ ህፃ ት አምባ የወጡ ታዳጊዎች ትምህርታቸውን እስኪጨርሱ ድረስ በአዲስ አበባ ሠ.ማ.ጉ.ቢሮ በኩል ድጎማ እንደከፈላቸው በተወሰነው መሠረት የሠ.ማ.ጉ.ቢሮው የክፍያ ጥያቄ ባለማቅረቡ ምክንያት ወጪው አንሶ ሊታይ ችሏል።